የኢትዮጵያውያን የጤና ድጋፍ ማህበር

የኢትዮጵያውያን የጤና ድጋፍ ማህበር በብሪታኒያ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የተለያዩ የጤና ድጋፍ (አገልግሎት) በድርጅቱ ቢሮ ውስጥና እንዲሁም ለተገልጋዩ አመቺ በሆነ የመስክ ስፍራ ይሰጣል። አገልግሎት ከምንሰጥባቸው ዋና ዋና የጤና ችግሮች ውስጥ የአእምሮ ፤ የአካል ና በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት የሚመጡ የጤና ችግሮች ይገኙበታል።

የድርጅቱ ዋና ዋና አገልግሎቶች፡

- ጤናን በሚመለከት የምክር አገልግሎት መስጠት (Counselling & advice)፤
- ሕመማንን ለመርዳት በቀጠሯቸው ላይ በመገኘት የቃል በቃል ትርጉም መስጠት፤
- ሕመማንን በቤታቸው፤ በሆስፒታል ና በመሳሰሉት ስፈራዎች መጠየቅ፤
- እንደበሽተኛው ሆኖ የጤና ባለሞያዎችን ማነጋገር፤ ስለበሽተኛው ሁኔታ ማስረዳት፤
- የጤና ና ጤና ነክ የሆኑ ጠቃሚ ጽሁፎችን መተርጎምና ማሰራጨት፤ በተጨማሪም ኮንደምና የመሳሰሉትን የአባለዘር በሽታ መከላከያዎችን በነጻ ማደል፤
- ሬዲዎንና ቴሌቪዥንን በመጠቀም ትምህርታዊ የሆኑ ጤና ነክ መረጃዎችን ማስተላለፍ፤
- ጤና ነክ ስብሰባዎችንና አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት፤
- በጤና ችግር ምክንያት የሚፈጠር ስራ አጥነትን ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር መፍትሄ እንዲያገኝ መርዳት፤
- በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ከሚኖሩበት ሃገር ህብረተሰብ ጋር በመተሳሰር አብሮ መኖር እንዲችሉ ማበረታታትና ማገዝ።

አገልግሎቱ የሚሰጠው የኢትዮጵያዊያንን ባህልና ቋንቋ በመከተል፤ ልምድ ባላቸው ሰራተኞችና በፍቃደኝነት ድርጅቱን በሚያገለግሉ ባለሞያዎች ሲሆን የእያንዳንዱ በሽተኛ መረጃም በሚስጥር ስለሚያዝ ለሌላ ወገን በፍጹም አይተላለፍም።

ቢደውሉልን ወይም መጥተው ቢያነጋግሩን በጣም ደስ ይለናል።

አድራሻችን፡ Ethiopian Health Support Association
Priory House, Kingsgate Place, London NW6 4TA

ስልክ፡ 020 7419 1972 ፋክስ፡ 020 7691 2385
ኢሜይል፡ admin@ethsa.co.uk ድረ ገጽ፡ www.ethsa.co.uk

በበለጠ ለመረዳት፡ አቶ ከፋለ አለሙን (የድርጅቱ አስተባባሪን) ወይም አቶ ሀይሌ ብዙአየሁን (የጤና አገልገሎት ሰራተኛን) ያነጋግሩ።